# ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ

በመምህር ልዑለ ቃል አካሉ

የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ተብሎ። ፍቅረ እግዚአብሔር ትምህርተ ሃይማኖት ነው። ፍቅረ ቢጽ ደግሞ ሥነ ምግባር ነው። የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረቱ የሕግ ፍጻሜ የሆነው ፍቅር ነው። ፍቅረ እግዚአብሔር በሁለት መልክ መታየት የሚችል ተናባቢ ወይም ተዛራፊ ቃል ነው። ትርጉሙም ሁለት ነው።

አንደኛው ፍቅረ እግዚአብሔር ማለት እግዚአብሔር እኛን የወደደበት ፍቅር፤ እግዚአብሔር ለኛ ያለው ፍቅር ማለት ነው። ይህ የሥነ ምግባራችን መሠረት ነው። «እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።» ዮሐ ፲፭፥፲፪።

ሁለተኛው ደግሞ እኛ እግዚአብሔርን የወደድንበት ወይም እኛ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ማለት ነው። ይህ ከእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ተመስርተን እግዚአብሔርን መውደዳችን የሃይማኖት መገለጫ ነው።

በወረቀት ወይም በሰሌዳ የተጻፈ ሕግ ለእግዚአብሔር የነበረውን ታማኝነትና ፍቅር ላጎደለው ሰው ሲሰጥ አሥር አንቀጾች ያሉት ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽን የሚያስተምር ሆኖ ነበር የተሰጠው። የመጀመሪያዎቹ አራት አንቀጾች ስለ ፍቅረ እግዚአብሔር ሲሆኑ የትምህርተ ሃይማኖት መሠረቶች ናቸው። የመጨረሻዎቹ ስድስት አንቀጾች ደግሞ ፍቅረ ቢጽ ላይ የተመሰረቱ ሲሆኑ የሥነ ምግባር መሠረቶች ናቸው። ዘጸ ፳፥፩-፲፯። ስለ ሥነ ምግባር ከመማራችን በፊት መሠረተ ምግባር ወተጋድሎ ስለሆነው ሃይማኖት በመጠኑ ማየት ይገባናል።

## ሃይማኖት

ፍችው፥- ሃይማኖት ሀይመነ ወይም አምነ - አመነ፣ ታመነ ከሚል የግእዝ ቃል የወጣ ዘር ሲሆን ፍችው ወይም ትርጉሙ ማመን፣ መታመን፣ አመኔታ፣ ጽኑ ተስፋ ማለት ነው።

ምስጢሩ፥ ተወክፎትን ያመለክታል። ማለትም ሃይማኖት ማለት መቀበል ማለት ነው። «ወለእለሰ ተወክፍዎ ወእለ አምኑ በስሙ ወሀቦሙ ስልጣነ ውሉደ እግዚአብሔር ይኩኑ» «ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው።» እንዳለ ወንጌል። ዮሐ ፩፥፲፪። «ተፈሥሒ እስመ ተወከፍኪ ቃሎ ለመልአክ» ማለትም «የመልአኩን ቃል ተቀብለሻልና (አምነሻልና) ደስ ይበልሽ» እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም «ወሶበ ተወክፎ ውእቱ ጻድቅ» ማለትም «ጻድቅ ዳዊት በተቀበለው (ባመነ) ጊዜ » እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም።

ሃይማኖት ተአዝዞትን ያመለክታል - ያም ማለት ሃይማኖት ማለት እግዚአብሔርን መታዘዝ መስማት ማለት ነው። «ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ» ማለትም «እንደቃልህ ይሁንልኝ» እንዳለች ድንግል ማርያም። ይህም ሃይማኖት መሆኑን ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ «ወብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር» ብላ ተርጉማዋለች። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር የተነገረልሽን ቃል የምታምኚ አንቺ ንእድ ክብርት ነሽ ማለት ነው። ሉቃስ ፩፥፴፰-፵፱።

ሃይማኖት ነበር፣ ነው፣ ሆኗል፣ ሆነ፣ ይሆናል፣ ተደረገ፣ ተደርጓል፣ ይደረጋል የሚል አንቀጽ የሚስማማው አማራጭ ወይም የተጋደመ ሃሳብ የማይስማማው ለመሃል ሰፋሪዎች የማይስማማ እና ያልተሰጠ የነፍስ የውስጥ ተወክፎት (ቅበላ) ነው።

እምነት (ሃይማኖት) የሁሉ መሠረት ነው፤ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም። (ዕብ ፲፩፥፮) እዚህ ላይ ከእምነት ጸጋ የቀደመው እምነት ራሱ የጸጋ ስጦታ ስለሆነ ነው። ማንም ቢሆን እግዚአብሔር ሰቦት፣ ራሱን ገልጦለት፣ በእርሱ ማመንን ሰጥቶት ካልሆነ በቀር በውሱን አእምሮው እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ አጥንቶ ስላላመነበት እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። የእግዚአብሔርም ቃል «የላከኝ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል ማንም የለም» ይላል።

«የመንፈስ ፍሬዎች.... እምነት የውሃት ...» (ገላ ፭፥፳፪) በማለት ይህንኑ አጽድቋል። እምነት የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንቀበልበት ውስጣዊ እደ (የልቡና እጅ) ነው። «እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ...» (ዕብ ፬፥፲፮) «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና» (ኤፌ ፪፥፰) በእምነታቸው እግዚአብሔርን ያስደሰቱትን እርሱም ስላመኑት ጸጋን ያበዛላቸውን የእምነት አርበኞች ታሪክ መመልከት ይጠቅማል (ዕብ ፲፩፥፩-፵)። እምነት የዘለዓለም ሕይወትን ያሰጣል (ዮሐ ፫፥፲፮)። እምነት ያጸድቀናል። (ሮሜ ፬፥፫-፭ ሮሜ ፲፥፱ ፤ ገላ ፪፥፲፮)

የአጋንንት እምነት ከሰዎች እምነት ልዩ ነው፤

- አጋንንት እግዚአብሔር እንዳለ ያምናሉ ( ዕብ ፪፥፲፱)

- ኢየሱስንም ያውቃሉ ሲያስጨንቃቸውም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ይመሰክራሉ። (ማቴ ፰፥፳፰-፳፱ ፤ ማር ፩፥፳፫-፳፰ ፫፥፲፩-፲፪ ፤ ማር ፭፥፩-፲ ፤ ሉቃ ፰፥፳፰-፳፱) ይህን ያህል ቢመሰክሩም ከእርሱ ጋራ መኖርን ስለማይፈልጉ «እናንተ ጋር ምን አለኝ» ይላሉ። የሰዎች እምነት ግን ደስ የሚለውን ደስ የሚያሰኘውን በማድረግ ከእርሱ ጋራ መኖርን ይፈልጋሉ። (ዮሐ ፮፥፳፰-፳፱ ፤ ማር ፭፤፯-፲፫)

- የአጋንንትና የተከታዮቹ እምነት የሞተ ነው። (ያዕ ፪፥፲፱-፳፮)። እኛም «ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ» ብንል ፈቃዱን ካላደረግን እንጎዳለን፤ እምነታችንም የአጋንንትና የተከታዮቹ እምነት ይሆንብናል።

## ሥነ ምግባር

ትርጉሙ - የበጎ ሥራዎች ዓይነትና ባሕርያት የተገለጸበት ቃል ነው። ሥነ ፍጥረት፣ ሥነ ሥርዓት፣ ሥነ ከዋክብት፣ ሥነ ልቡና፣ እንደሚሉት ቃላት ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያለው ቃል ነው።

መሪ ጥቅስ፥
«እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።» ኤፌ ፪፥፲

ሮሜ 7፤15

መልካም ሥራ
እምነትን ያለ መልካም ሥራ መግለጽ አይቻልም፤ (ያዕ ፪፥፲፰-፳፩) ያለ እምነትም መልካም ሥራ መሥራት አይቻልም። ማለትም መልካም ሥራ የማይሠራ አማኝ አይደለም። ያላመነም መልካም ሥራ አይኖረውም። በመሆኑም እምነት ያለ ሥራ የሞተ ሥራም ያለ እምነት የሞተ ነው። (ያዕ ፪፥፲፰-፳፮) አንድ ክርስቲያን መልካም ሥራ እንዲኖረው አስቀድሞ ከበረሃው ወይራ ተቆርጦ በመልካም ወይራ ላይ መዳቀል አለበት (ሮሜ ፲፩፤ ፳፬)። "ከፉ ዛፍ መልካም ማፍራት አይቻለውም ፍሬው መልካም ይሆን ዘንድ ዛፍዋን መልካም አድርጉ" (ማቴ ፯፥፳ ፲፪፥፴፫) ተብሎ እንደተጻፈ።